
ነገረ ክርስቶስ

ምዕራፍ 3



አዘጋጅ፡- መምህር በትረ ማርያም አበባው

(የመጻሕፍተ ሊቃውንት፣ የመጻሕፍተ ብሉያትና የመጻሕፍተ መነኮሳት ትርጓሜ መምህር & BSC CIVIL ENGINEERING)

ክፍል ፩

የምሥጢረ ሥጋዌ ትምህርት መሠረት ምሥጢረ ሥላሴ ነው። ሥላሴ ማለት "ሦስትነት" ማለት ነው። ቅድስት ሥላሴ ስንል ደግሞ ልዩ ሦስትነት ተብሎ ይተረጎማል። ይኽውም ከፍጡራን ሦስትነት የተለየ ሦስትነት ለማለት ነው። በባሕርይ አንድ የሆነ እግዚአብሔር በአካል ሦስት መሆኑን የምንማማርበት ትምህርት ምሥጢረ ሥላሴ ይባላል።

ልዩ ሦስት ያሰኛቸው ነገር ምንድን ነው?

አንደኛ አንዱ አካል በአንዱ አካል ህልው መሆኑ ነው። ይኽውም እኛ ሰዎች ሦስት ብንባል አንዳችን በአንዳችን ላይ አንኖርም። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ግን አንዱ አካል በአንዱ አካል ህልው ሆነው ይኖራሉ። ይህንንም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "እኔ በአብ እንዳለኹ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ ባይኾንስ ስለ ራሱ ስለ ሥራው እመኑኝ" ብሎ ገልጾታል (ዮሐ. ፲፬፣፲፩)። ሊቅም "ነአምን ከመ አብ በወልድ ወበመንፈስ ቅዱስ ወወልድ በአብ ወበመንፈስ ቅዱስ ወመንፈስ ቅዱስ በአብ ወወልድ" ብሎ ገልጾታል (ሃይ.አበ.፲፩)።

ሁለተኛ መገነዛዘባቸው ነው። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስን ልዩ ሦስት ያሰኛቸው መገነዛዘባቸው ነው። በፍጡራን ዘንድ አንዱ በአንዱ ህልው ሊሆን ይችላል። ነገር ግን አንዱ አንዱን ገንዘብ አያደርገውም። ለምሳሌ ሦስት አንፖሎችን በአንድ ቤት ውስጥ ብናበራቸው የአንዱ ብርሃን ከአንዱ ብርሃን ህልው ይሆናል። ነገር ግን ብርሃናቱ መገነዛዘብ የላቸውም። የፀሐይ ብርሃን በሕዋ ካለው አየር ጋር በህልውና አንድ ይሆናሉ። ነገር ግን ገንዘብ አይደራረጉም። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ግን በህልውና አንድ መሆን ብቻ ሳይሆን በከዊን መገነዛዘብ አላቸው። የአብ የሆነው ሁሉ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ነው፣ የወልድ የሆነው ሁሉ የአብ የመንፈስ ቅዱስ ነው፣ የመንፈስ ቅዱስ የሆነው ሁሉ የአብ የወልድ ነው። ይኽውም ከግብረ ልደት ውጭ ነው። "ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው" እንዲል (ዮሐ. ፲፮፣፲፭)። ሦስቱ አካላት የሚገነዛዘቡት ደግሞ በከዊናቸው አማካኝነት ነው። የአብ ከዊን ልብነት፣ የወልድ ከዊን ቃልነት፣ የመንፈስ ቅዱስ ከዊን እስትንፋስነት ነው። አብ ልብ ሆኖ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስም ልባቸው ነው። ወልድ ቃል ሆኖ ለአብ ለመንፈስ ቅዱስም ቃላቸው ነው። መንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ ሆኖ ለአብና ለወልድም እስትንፋሳቸው ነው። ስለዚህ ሦስትነታቸው መገነዛዘብ ስላለው ልዩ ሦስትነት ተብሏል።

ሦስተኛ በቅድምና አንድ መሆናቸው:- ወልድና መንፈስ ቅዱስን ከአብ የተገኙ ብንላቸውም መገኘታቸው (ተረክቧቸው) መቀዳደም ሳይኖርበት ነው። ይኽውም አብ ቀድሞ ኖሮ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በኋላ የተገኙ አይደሉም። የፀሐይ ብርሃንና ሙቀት ከፀሐይ ክበብ ሲገኙ ምንም እንኳ ተገኙ ብለን ብንናገርም ቀድሞውንም ከክበቡ እንዳልተለዩና ክበቡ ያለ ብርሃንና ሙቀት ቀድሞ የነበረበት ዘመን እንዳልነበረው ያለ ነው። "ኢሀሎ አብ ግሙራ ዘመነ እምነ አዝማን እንበለ ወልድ ወኢወልድ ዘእንበለ መንፈስ ቅዱስ" እንዲል (ሃይ.አበ. ፷፱)። እንዲሁም "አሐቲ ይእቲ ቅድምናሆሙ ለሥላሴ" ይላል (ሃይ.አበ. ፶፩)። አብርሃም ይስሐቅንና ያዕቆብን ሦስት ብንላቸው በዘመን መቀዳደምም አለባቸው። ያዕቆብ ከይስሐቅ ይስሐቅ ከአብርሃም ተወልደዋል።

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስን ሦስት ስንል ግን በዘመን መቀዳደም የሌለባቸው ሦስት ስለሆኑ ልዩ ሦስት እንላቸዋለን።

የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ሦስትነታቸው በምን በምን ነው?

፩ኛ በአካል፦ የአብ የራሱ ፍጹም ገጽ ፍጹም መልክ አለው፣ የወልድም የራሱ ፍጹም ገጽ ፍጹም መልክ አለው፣ የመንፈስ ቅዱስም የራሱ ፍጹም ገጽ ፍጹም መልክ አለው። "ነአምን በሠለስቱ አካላት ፍጹማን ወበሠለስቱ ገዳት ፍጹማን ዕሩያነ መልክዕ" እንዲል (ሃይ.አበ. ፻፲)። ሦስቱ አካላት በመልክም በምልዐትም በርቀትም የተካከሉ ናቸው። ሦስቱ አካላትም ስማቸው አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ነው (ማቴ. ፳፰፣፲፱)። እነዚህ አካላት እጅ፣ እግር፣ ዓይንና በጠቅላላው በቅዱሳት መጻሕፍት የተጠቀሱ አካላት አሏቸው። ነገር ግን እጃቸው፣ እግራቸው፣ ዓይናቸው እና ሌሎችም አካሎቻቸው ወሰን የሌለባቸውና ከሰው ጎሊና መታሰብ በላይ ናቸው። ሁሉ በሁሉ አሉ። "ወዘይቤሉ መጻሕፍት ከመቦ ለእግዚአብሔር አዕይንት ወአዕዛን ወኵሉ ዘተብህለ እለተርፉ በእንተ እግዚአብሔር ነአምን ከመእሙን ወጽድቅ ውእቱ ወባሕቱ ኢይትረከብ ወኢይትኄለይ" እንዲል (ሃይ.አበ.፲፱)።

፪ኛ በአካላዊ ግብር፦ የአብ አካላዊ ግብር መውለድ ማሥረጽ ነው፣ የወልድ አካላዊ ግብር መወለድ ነው፣ የመንፈስ ቅዱስ አካላዊ ግብር መሥረጽ ነው (ሃይ.አበ.፲)። ወልድ ከአብ ስለተወለደ የአብ የባሕርይ ልጅ (ወልደ አብ) ይባላል (ዮሐ. ፲፣፴፮)። መንፈስ ቅዱስም ከአብ ስለሠረጸ ከአብ የሚወጣ ይባላል (ዮሐ.፲፭፣፳፮)። በአካላዊ ግብር ስማቸውም አብ ወላዲ አሥራጊ፣ ወልድ ተወላዲ፣ መንፈስ ቅዱስ ሠራጊ ይባላሉ።

፫ኛ በከዊን፦ አብ አካላዊ ልብ ነው፣ ወልድ አካላዊ ቃል ነው፣ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ እስትንፋስ ነው። ሦስቱ አካላት በአካል ሲለያዩ የሚገነዛዘቡት ደግሞ በከዊን ነው። ስለዚህ ኵነታት ተገናዝቦ እንጂ እንደ አካላት ተሌልዮ አይነገርላቸውም። የሦስቱ ኵነታት ተገናዝቦ መለኮት ወይም ባሕርይ እየተባለ ይጠራል። "ይትዋሐዱ በመለኮት ወይትሌለዩ በአካላት" እንዲል (ሃይ.አበ.፶፯)።

የአብ የወልድ የመንፈስቅዱስ አንድነታቸውስ በምንድን ነው?

አንደኛ በባሕርይ፦ ባሕርይ ማለት አካል ያልሆነ ነገር ግን አካላዊ የሆነ አካል የሚገልጠው የአካል መሠረት ማለት ነው። ሦስቱ አካላት በባሕርይ አንድ ናቸው። ባሕርይ ሦስቱን አካላት የሚያገናዝብ ነው። አንድም የሦስቱ አካላት መገናዘብ ባሕርይ ነው። በደንብ መረዳትና ማስተዋል ያለብን ባሕርይ ከሦስቱ አካላት ውጭ የሆነ አራተኛ ማንነት አይደለም። የሦስቱ አካላት በከዊን መገናዘብ ነው እንጂ። ኪራኮስ የተባለ ሊቅ እንደተናገረው አካል ያለ ባሕርይ ባሕርይ ያለ አካል አይገኝም። ይህም ማለት ባሕርይ የሌለው አካል፣ አካል የሌለው ባሕርይ የለም ማለት ነው። "ኢይደሉ ይኩን ህላዌ ዘእንበለ አካል። ወኢይደሉ ይትረከብ አካል ዘእንበለ አምሳሉ ለአካል። ባሕርይ ያለ አካል አካል ያለ ባሕርይ ይገኝ ዘንድ አይገባም" እንዲል (ሃይ.አበ.፶፩፣፶፰)። የሦስቱ አካላት ባሕርይ ደግሞ አንድ ነው። ከባሕርይ የወጣ አካል ደግሞ የለም።

ሁለተኛ በግብረ ባሕርይ አንድ ናቸው። ግብረ ባሕርይ የሚባለው መፍጠርን፣ መግዛትን፣ ንጉሥ መሆንን፣ ዘለዓለማዊነትን፣ ሁሉን ቻይነትን በጠቅላላው አምላካዊ ሥራዎችን ያመለክታል። ማንኛውንም አምላካዊ ሥራ ሦስቱ አካላት ተገናዝበው የሚሠሩት ስለሆነ በአምላካዊ ሥራ ሦስቱ አንድ ናቸው። በግብረ ባሕርይ አብ የሚሠራውን ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይሠሩታል፣ ወልድ የሚሠራውን አብ መንፈስ ቅዱስ ይሠሩታል፣ መንፈስ ቅዱስ የሚሠራውን አብ ወልድ ይሠሩታል። "ወአኮ አብ በርእሱ ባሕቲቱ ዘይገብር ወወልድኒ አኮ በርእሱ ባሕቲቱ ዘይገብር ወመንፈስ ቅዱስኒ አኮ በርእሱ ባሕቲቱ ዘይገብር። ወምግባሮሙኒ አሐዱ እስመ አሐዱ መለኮቶሙ" እንዲል (ሃይ.አበ.፲፩)። በግብረ ባሕርይ ሦስቱ አካላት አንድ ናቸው። በምሥጢረ ሥጋዌ ሥጋን አምላክ በማድረግ፣ በማዋሐድ፣ በማክበር ሦስቱ አንድ ናቸው (ሃይ. አበ. ፻፳፬፣፻፴)። ለሥጋ በተለየ አካሉ ክብር መሆን ግን የወልድ ነው። ይኽውም ሰው የሆነው በተለየ አካሉ ወልድ ስለሆነ ነው። ሥጋም ወልድን ሆነ እንጂ አብን መንፈስ ቅዱስን አልሆነምና ነው። ይህን ትቶ መንፈስ ቅዱስ ለሥጋ ክብር ሆነው ማለት ግን መንፈስ ቅዱስን ሰው ሆነ የሚያሰኝ ትልቅ ክሕደት ነው። ሃይ.አበ. ፻፳፭፣፻፻ "እመቦ ዘይብል በእንተ አሐዱ እግዚአብሔር እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመ ለሊሁ ክብረ በመንፈስ ቅዱስ ወተሰብሐ ውጉዘ ለይኩን" እንዲል።

ክፍል ፪

በአንድነቱ ምንታዌ በሦስትነቱ ርባዔ የለበትም ስለማለት

በጊዜ ተዋሕዶ አምላክ ሰው ሆነ፣ ሰው አምላክ ሆነ። ይኽውም በተዋሕዶ በተዓቅቦ ነው። ተዓቅቦ ማለት አለመጠፋፋትን የሚገልጽ ቃል ሲሆን ሚጠትን፣ ውላጤን የሚያጠፋ አነጋገር ነው። ተዋሕዶ ማለት ደግሞ ምንታዌን፣ ኀድረትን፣ ትድምርትን፣ ፍልጠትን የሚያጠፋ አነጋገር ነው። ሰዎች ተዓቅቦን ይዘው ምንታዌና ኀድረት እንዳይሉ ተዋሐደ ያሰኝባቸዋል። ተዋሐደ የሚለውን ይዘው ተለወጠ እንዳይሉ ተዓቅቦ ይልባቸዋል። ስለዚህ የቤተክርስቲያን አስተምህሮ ተዋሕዶ በተዓቅቦ የሚል ነው። ኀደረን ከሓድያን ሲጠቅሱት እንደኀዳሪና እንደማኀደር አድርገው ይጠቅሱታል። ቅዱሳት መጻሕፍት ኀደረን ሲጠቅሱ ግን ተዋሐደ ብለው ያስተረጉማሉ። "ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ ዐደረ" ባለ ጊዜ ሆነም አደረም ተዋሐደ ተብለው ይተረጎማሉ (ዮሐ.፩፣፲፬)። ሆነና አደረ ተዋሕዶ በተዓቅቦን ያመለክታሉ። መተርጉማን ሊቃውንተ ኢትዮጵያ በትርጓሜ እንደገለጹት ከሓድያን ኮነን ይዘው ተለወጠ እንዳይሉ ኀደረ ይልባቸዋል። ኀደረን ይዘው አደረበት እንዳይሉ ኮነ ይልባቸዋል። ስለዚህ ኮነና ኀደረ ይጠባበቃሉ የሚሉት ይህንን ነው። ትድምርት የሚለውም ተዋሕዶ ተብሎ የሚተረጎምበት ወቅት አለ። "ነአምን በትድምርተ መለኮት ወትስብእት። ኵለንታሁኬ ለቃል ወኵለንታሁ ለትስብእት ከመ ተደመረ ነአምን" እንዲል (ድርሳነ ቂርሎስ ፲፰)። በዚህ ጊዜ ትድምርት ተዋሕዶ፣ ተደመረ ተዋሐደ ተብሎ እንደተተረጎመ ለቡ። እንበለ ትድምርት ባለ ጊዜ ግን ትድምርት ተዋሕዶን አያመለክትም። ስለዚህ እንደ ቃሉ አገባብ ማየት ተገቢ ነው።

አንዳንዶች ተዓቅቦ ካለ ምንታዌን (የባሕርይ ሁለትነትን) ያመጣል ብለው ይናገራሉ። ይህ ከሆነ ደግሞ የካቶሊክ አስተምህሮ አንድ አካል ሁለት ባሕርይ ያለው ያስኬዳል ብለው ይናገራሉ።

ነገር ግን እንዲህም ካሉ ወደ ንስጥሮስ ክሕደት ይመራቸዋል እንጂ ግማሽ ታቦት ግማሽ ጣዖት የሆነ የተሳሳተ አስተምህሯቸውን አይደግፍላቸውም። ምክንያቱም ተዓቅቦ የሚነገር ለባሕርይ ብቻ ሳይሆን ለአካልም ስለሆነ በግድ ሁለት አካል ስለሚያስኝባቸው ነው። ምንታዌ የሚኖረው ተዋሕዶ በሌለበት ተዓቅቦ ነው እንጂ ተዋሕዶ ባለበት ተዓቅቦ አይደለም። ተዋሕዶ ብለን ተዓቅቦን ባንጠቅስ ውላጤን ያመጣል። ተዓቅቦ ብለን ተዋሕዶን ባንጠቅስ የንስጥሮስን ክሕደት (ምንታዌን) ያመጣል። እኛ ግን አምላክ ሰው ሰው አምላክ ሲሆን በተዋሕዶ በተዓቅቦ ነው ስለምንል በአንድነቱ ላይ ምንታዌ በሦስትነቱ ላይ ርባዔ የለም እንላለን። ከተዋሕዶ በኋላ አንዱን ክርስቶስን ለሁለት አንከፍለውም። "ንሕነሰ ኢንቤ ክልኤቱ እምድኅረ ትድምርት። አላ ባሕቱ ንሌቡ ከመ እምክልኤ ህላዌ ተደመረ አሐዱ ክርስቶስ ቃል" እንዲል (ድርሳነ ቂርሎስ ፳፫)። ቃል የራሱን ባሕርይ እንደያዘ የሥጋን ባሕርይ ገንዘብ በማድረጉ በባሕርየ ሥላሴ ላይ ምንታዌን አላመጣም። ምክንያቱም ቃልና ሥጋ በተዋሕዶ አንድ ሆኑ እንጂ እየራሳቸው ሆነው ሁለት አልሆኑምና ነው። ቃል የራሱን አካል እንደያዘ አካለ ሥጋን ገንዘብ በማድረጉ በአካላት ላይ አራተኛ አልሆነም። ምክንያቱም አካለ ቃልና አካለ ሥጋ በተዋሕዶ አንድ ሆነዋልና ነው። ይህንን ሊቅ በሃይማኖተ አበው "ወኢወሰከ ጕልቈ ራብዐ ወኢካልዐ ገጸ" ብሎ ገልጾታል (ሃይ.አበ.፶፩)።

ክፍል ፫

ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስን ዐረገ፣ ወረደ ስለማለት

ወልደ እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ ያለና የሚኖር መሆኑ ይታወቃል። በሁሉ ቦታ ያለ አካልን ወረደ ዐረገ ማለት ምን ማለት ነው? አንድን አካል ዐረገ ስንል በቃላዊ ትርጓሜ ከታች ኖሮ ሳለ ከላይ ሳይኖር ቀርቶ ከታች ወደላይ ወጣ ማለት መሆኑ ግልጽ ነው። በዚህን ጊዜ ከላይ ሲገኝ ከታች መታጣት አለበት። ወረደ ማለትም በአንጻሩ ከላይ ኖሮ ቆይቶ ከታች ሳይገኝ ኖሮ ከላይ ወደታች ወረደ ማለት ነው። ይህን ጊዜ ከታች ሲገኝ ከላይ መታጣት አለበት። ወልደ እግዚአብሔርን ከሰማየ ሰማያት ወረደ ከድንግል ማርያም ተወለደ ስንል ግን ወረደ የሚለው ቃል ሰው ሆነ ተብሎ ይተረጎማል። ሰው መሆንን ርደት ብሎት ነው። ወረደ በመጽሐፍ ቅዱስ ለእግዚአብሔር ሲነገር ብዙ ትርጉም አለው። "እግዚአብሔርም የአዳም ልጆች የሠሩትን ከተማና ግንብ ለማየት ወረደ" ሲል ምሥጢሩ መዓትን ያመለክታል (ዘፍ.፲፩፣፭)። "እግዚአብሔርም በሲና ተራራ ላይ ወደ ተራራው ራስ ወረደ" ሲል ደግሞ በዘፈቀደ መገለጥን ያመለክታል (ዘፀ.፲፱፣፳፣ ዘጕ. ፲፪፣፭፣ ሉቃ. ፫፣፳፪)። "እግዚአብሔርም ስለ እኔ በጎያላን ላይ ወረደ" ሲል ደግሞ ረድኤት መስጠትን ያመለክታል (መሳ.፭፣፲፫፣ መሳ. ፲፩፣፲፱፣ ዮሐ.፮፣፴፱፣ የሐዋ. ሥራ ፩፣፲)። "ወደዚያም ከሪብታ በደረሰ ጊዜ፥ እንሆ፥ የነቢያት ጉባኤ አገኙት የእግዚአብሔርም መንፈስ በኀይል ወረደበት፥ በመካከላቸውም ትንቢት ተናገረ" ሲል ጸጋ መስጠትን ያመለክታል (፩ኛ ሳሙ. ፲፣፲፣ የሐዋ. ሥራ ፲፩፣፲፭፣ የሐዋ. ሥራ ፲፱፣፮)። ክርስቶስ ሰው በሆነ ጊዜ በተዋሐደው ሥጋ ከአንድ ቦታ ወደ አንድ ቦታ መሄዱን ለመግለጽ ወረደ እየተባለ የተገለጸበት ጊዜም አለ። "ከተራራም በወረደ ጊዜ ብዙ ሕዝብ ተከተሉት" እንዲል (ማቴ.፰፣፩)። ወልደ እግዚአብሔርን በምሥጢረ ሥጋዌ ወረደ ስንለው ሰው ሆነ ማለታችን ነው። ይህንን ከሚያስረዱን ጥቅሶች አንዱ "ከሰማይም ከወረደ በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም

የለም፥ እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው" የሚለው ነው (ዮሐ.፫፣፲፫)። ከሰማይ ወረደ መባሉ አምላክ ሰው ሆነ ማለት ነው። በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው ማለት ደግሞ ሰው አምላክ ሆነ ማለት ነው። "ሰው ከርሱ በልቶ እንዳይሞት ከሰማይ አሁን የወረደ እንጀራ ይህ ነው" የሚለው ቃልም ይህንኑ ያስረዳል (ዮሐ. ፮፣፶)። ወልደ እግዚአብሔር ከሰማይ የወረደ መባሉ ሰው መሆኑ ለመግለጽ ነው። የሕይወት እንጀራ መባሉ ሰው አምላክ መሆኑን ያመለክታል።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ለቃል ርደት ለሥጋ ዕርገት ምክንያት ሆነች እንላታለን። ይህ አገላለጽ የቃል ርደት የተባለው የቃልን ሰው መሆን ለመግለጽ ሲሆን፣ የሥጋ ዕርገት የተባለው ደግሞ የሰው አምላክ መሆን ነው። ዐረገ የሚለው ቃል ለፍጡራን ሲነገር ከታች ታጥቶ ከላይ መገኘትን ያመለክታል (መሳ.፲፫፣፳)። ክርስቶስ ለተዋሐደው ሥጋ ሲነገር ግን አምላክ ሆነ ተብሎ ይተረጎማል። ይህም የሆነው በጊዜ ተዋሕዶ ነው። አባቶቻችን ሊቃውንት በትርጓሜያቸው የቃል ዕርገት በአርባ ቀን፣ የሥጋ ዕርገት በማኅፀን የሚሉት ይህንን ነው (ሃይ.አበ.፲፯፣፱ ሐተታ)። ቃልን ወረደ ስንለው ሰው ሆነ ሥጋን ገንዘቡ አደረገ ማለታችን ነው። ይህንን ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ "አኮ ዘፈለሰ እመካን ውስተ መካን ከመ መላእክት እሙንቱሰ ይትነጥኡ እመካኖሙ ሶበ ይትፌነዉ ለመልእክት" ብሎታል። ትርጉሙ መላእክት ለመልእክት ከሰማይ ወደ ምድር ሲላኩ ከምድር ይገኛሉ ከሰማይ ይታጣሉ። ከምድር ወደ ሰማይ ሲያርጉ ከምድር ይታጣሉ ከሰማይ ይገኛሉ። እርሱ ጌታ ግን ወረደ ስንለው ምልዐቱን ሳይለቅ ውስን ሥጋን ገንዘብ አደረገ ማለት ነው። ሊቃውንት የሥጋ ዕርገት በማኅፀን ያሉት የርኅቀት ያይደለ የርቀት ዕርገት ነው። ይኽውም ሥጋ ግዙፍነትን ሳይለቅ ረቂቅ ቃልን ገንዘቡ በማድረጉ የተነገረ ቃል ነው። የቃል ዕርገት በአርባ ቀን የሚባለው ደግሞ ከትንሣኤ በአርባኛው ቀን ያረገውን ዕርገት ሲሆን ይኽውም ቃል በሥጋ የርቀት ያይደለ የርኅቀት ዕርገት ማረጉን የሚያመለክት ቃል ነው። ክቡር አንባቢ ሆይ የሥጋ ዕርገት የቃል ዕርገት ሲባል ስትሰማ ምንታዌ እንዳይመስልህ ተጠንቀቅ። የሥጋ ዕርገት ስንል በቃል ማለታችን እንደሆነ የቃል ዕርገት ስንልም በሥጋ ማለታችን እንደሆነ አስተውል። ቅዱሳን ቢያርጉ በእግዚአብሔር ኃይል ነው። ክርስቶስን ዐረገ ስንል ግን በራሱ ሥልጣን ዐረገ ማለታችን እንደሆነ ለቡ። "ኃይላት አዕረግዎ ለኤልያስ ኀበ ተአዘዙ። ወቃለ እግዚአብሔር ዋሕድ ለሊሁ ዐርገ በሥልጣኑ እስመ እግዚአ ኃይላት ውእቱ" እንዲል (ሃይ.አበ.፷፯)።

ክፍል ፬

በእንተ ሥጋሁ ወደሙ ለክርስቶስ

የምንቀበለው ሥጋና ደም አብ ልቡ መንፈስ ቅዱስ እስትንፋሱ የሆነውን ነው። ነፍስ የተለየው መለኮት የተዋሐደውን ሥጋና ደም እንቀበላለን። የምንቀበለው ሥጋ መለኮትን (የመለኮትን ሥጋ) ነው። በዚህ ጊዜ መለኮት የሚለው ወልደ እግዚአብሔር ቃለ አብ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን መረዳት ይገባል። ለአብ ሥጋ የለውምና። ለመንፈስ ቅዱስም ሥጋ የለውምና። ቃለ አብ ግን በጊዜ ተዋሕዶ የሥጋን ገንዘብ ገንዘብ በማድረጉ ሥጋዬ ይላል። ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር ሥጋዬን ብሉ፣ ደሜን ጠጡ ብሏል (ማቴ.፳፮፣፳፮)። የዕሩቅ ብእሲን ሥጋ መብላት

በሽታን እንደሚያመጣ መተርጉማን ገልጸዋል። ክርስቶስ ግን አምላክ ወሰብእ በመሆኑ ሥጋው መለኮትን ገንዘብ ያደረገ በመሆኑ ዘለዓለማዊ ሕይወትን ይሰጠናል። አዳምና ሔዋን ዕፀ በለስን ከበላችሁ የሞት ሞትን ትሞታላችሁ ተብለው ነበር። የተከለከሉትንም በልተው ሞትን ሞቱ። በኋላ ወልደ እግዚአብሔር ከድንግል ማርያም ተወልዶ ደግሞ እኛን የአዳም ልጆችን ደሜን ካልጠጣችሁ ሥጋዬን ካልበላችሁ የዘለዓለም ሕይወትን አታገኙም አለን። ስለዚህ ሕይወት የሚሆንን ሥጋውንና ደሙን ባንቀበል በራሳችን ላይ ፍዳን እናመጣለን።

ሥጋውን ደሙን መቀበል ከኃጢአት ያነጻል (ራእ.፩፣፭)። ብዙዎች ሥጋውን ደሙን መቀበል ለሕፃናት ወይም ለሽማግሌዎች ወይም ለካህናት ብቻ የተፈቀደ አስመስለው ይናገራሉ። ነገር ግን ሥጋው ደሙ በእርሱ ላመኑት ሁሉ የተሰጠ መሆኑን መረዳት ይገባል። ስለዚህ ማናችንም ብንሆን ንስሓ ገብተን ሥጋውን ደሙን መቀበል ይገባናል። ከጥምቀት በፊት የተሠራ ኃጢአት በጥምቀት ይሠረያል። ከጥምቀት በኋላ የተሠራ ኃጢአት ደግሞ ንስሓ ገብተን ሥጋውን ደሙን በመቀበል ይሠረያል። ሥጋውን ደሙን ስንቀበል ሥጋው ደሙ የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ነው። የምንቀበለውና የምናገኘው ጸጋ ግን የሦስቱም ማለትም የአብም የወልደም የመንፈስ ቅዱስም ነው። የምንወስደው መድኃኒት የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው። የምናገኘው ድኅነት ግን የሦስቱም ነው። ሥጋውን ደሙን ስንቀበል ግን በድፍረት ሳይሆን በትሕትና ሆነን፣ ንስሓ ገብተን መሆን አለበት። እንዲህ ካልሆነ በራሳችን ላይ መቅሠፍትን መሰብሰብ ይሆንብናል። "ስለዚህ፥ ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ፥ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት። ሰው ግን ራሱን ይፈትን፥ እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ ከጽዋውም ይጠጣ። ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና፥ ይጠጣልና" እንዲል (፩ኛ ቆሮ. ፲፩፣፳፯-፳፱)።

ክፍል ፭

ጥንተ አብሶን በተመለከተ

ከትርጉሙ እንነሳ ጥንተ አብሶ የሚለው ቃል ከሁለት ቃላት የተመሠረተ ቃል ነው። እነዚህም ጥንት እና አብሶ ናቸው። ጥንት ማለት መጀመሪያ ማለት ሲሆን አብሶ የሚለው ቃል ደግሞ አበሰ-በደለ ከሚለው የግእዝ ቃል የወጣ ንዑስ አንቀፅ ነው ትርጉሙም መበደል፣ በደል ማለት ነው። ስለዚህ ጥንተ አብሶ ማለት የበደል መጀመሪያ ማለት ነው። ይኽውም አዳም የበደለው የመጀመሪያው በደል ነው። ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር መልክና አርአያ ነው። እግዚአብሔር ነጻነት ያለው አምላክ እንደመሆኑ ሰውንም በነጻነት ይኖር ዘንድ ፈጥሮታል። እግዚአብሔር አዳምን ዕፀ በለስን እንዳይበላ አዝዞት ነበር (ዘፍ.፪፣፲፯)። ሰው በነጻነት የተፈጠረ ነጻ ፈቃድ ያለው ስለሆነ ለበደለው በደል ኃላፊነቱን የሚወስድ ራሱ ነው። ስለዚህ የሰው በደል የራሱ ነፃ ፈቃድ ውጤት ነው። የውጭ ጸሐፍት "Human sin, past or present, is one of the possible consequences of the free will that God has given to each of us" ይሉታል። አዳም በፈቃዱ ዕፀ በለስን በልቶ ወደቀ። ወደቀ ስንልም ልጅነቱን አጣ፣ ገነትን አጣ ማለታችን ነው። እነዚህ ነገሮች የጥንተ አብሶ ውጤቶች ናቸው። የውጭ ጸሐፍት "When Adam lost Paradise both he and Eve had not had the opportunity to enter into

their full inheritance as a children of God" የሚሉት ይህንን ነው። የአዳም ልጆችም እስከ ክርስቶስ ድረስ ያሉት አዳም በበደለው በደል ምክንያት ሁሉም ገነትን አጥተው በሲኦል ይሰቃዩ ነበር። አዳምም ልጆቹን ሲወልድ ዘሩን ምክንያት አድርጎ የሚወለደውን ልጅ ሰይጣን ይቆራኘውና እስከ ዕለተ ሞቱ ኃጢአት ሲያሠራው ይኖር ነበር። ጌታ ግን ያለወንድ ዘንድ ከድንግል ማርያም ተወልዶ መንገድ ለውጦበታል። ጌታ ሲፀነስ ቁራኝነት ጠፋልን። በክርስቶስ ሰው መሆን ቀድሞ የነበረብን መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ ራቀልን (የኃሙስ ውዳሴ ማርያም ትምክህተን ተመልከት)። በብሉይ ኪዳን ጻድቃን ብንሆንኳ መርገሙ ስለነበረ ሁላችንም ሲኦል እንገባ ነበር። "ሁላችን እንደ ርኩስ ሰው ሆነናል፥ ጽድቃችንም ሁሉ እንደ መርገም ጨርቅ ነው ሁላችንም እንደ ቅጠል ረግፈናል፥ በደላችንም እንደ ነፋስ ወስዶናል" እንዲል (ኢሳ. ፷፬፣፮)። ጻድቃን ሁሉ ወደሲኦል ቢገቡም ከዚያ እሳቱ እንዳያቃጥላቸው በረድኤተ እግዚአብሔር ይጠበቁ ነበር። "ጻድቃንሰ ውስተ እደ እግዚአብሔር ወኢለከፈቶሙ እሳተ ገሐነም" እንዲል።

ቀድሞም ቢሆን የአዳም መርገሙ እንጂ ኃጢአቱ ወደ ሰው አልተላለፈም። ኃጢአት ከአባት ወደ ልጅ አይተላለፍምና። "ነጢአትን የምትሠራ ነፍስ እርሷ ትሞታለች ልጅ የአባቱን ኀጢአት አይሸከምም፥ አባትም የልጁን ኀጢአት አይሸከምም የጻድቁ ጽድቅ በራሱ ላይ ይሆናል፥ የኀጢአተኛውም ኀጢአት በራሱ ላይ ይሆናል" እንዲል (ሕዝ.፲፰፣፳)። መርገሙ ግን ተላልፎብን ይኖር ነበር። ጌታ ሰው ሆኖ በመስቀል ተሰቅሎ ግን ይህንን መርገም (ፍዳ) አጠፋልን። "ወደምሰሰ መጽሐፈ ዕዳሆሙ ለአዳም ወለሔዋን" እንዲል (የሰኞ ውዳሴ ማርያም)። ይኽውም ፍዳን መርገምን አጠፋልን ማለት ነው። መርገመ አዳም ላዕለ ውሉድ ወልደ እግዚአብሔር ሰው ከሆነ በኋላ ቀርቶልናል። ከዚህ በኋላ ሰው ኃጢአት ቢሠራ በራሱ ኃጢአት ይጠየቃል እንጂ በአዳም በደል ምክንያት ወደ ሲኦል አይወርድም። አዳም ልጅነቱን አጥቶ ይኖር ነበር። ጌታ ሰው ሆኖ ልጅነቱን መልሶለታል። ከዕለተ ዓርብ በፊት በሲኦል የነበሩ ነፍሳት ሁሉ ልጅነትን አግኝተው ወደገነት ተመልሰዋል። ጌታ በአፀደ ነፍስ ሄዶ ቀኝ እጁን ቢያሳያቸው ያ ጥምቀት ሆኗቸው ተመልሰዋል። "የማነ እዴየ መጠውክምሙ ወኮነቶሙ ጥምቀተ" እንዲል። በብሉይ ዘመን የነበሩ ሰዎች ልጅነትን ለማግኘት እድል አልነበራቸውም። ከዚህ በኋላ ላለ የዓለም ሕዝብ ግን ልጅነትን ያገኝ ዘንድና ክቡር ሆኖ ይኖር ዘንድ እድል ተሰጥቶታል። የውጭ ጸሐፍት "In Christ we now have that opportunity, not only to be saved from death and hell, but also to be glorified by his life" እያሉ ይገልጹታል።

አሁን ላይ ሰው ነጻ ፈቃዱን ተጠቅሞ ተጠምቆ የእግዚአብሔር ልጅ መሆን ይችላል። ይህን ማድረግ ሳይችል ቢቀር ግን በአዳም መርገም ተይዞ ወደቀ አንልም። ራሱ በፈቃዱ መርገምን መረጠ ይባላል እንጂ። በአዳም ምክንያት ሞት ወደዓለም የገባ የነበረ ቢሆንም በክርስቶስ ምክንያት ደግሞ ዘለዓለማዊ ሕይወት ሆነልን። "ስለዚህ ምክንያት፥ ኀጢአት ባንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ፥ በኀጢአትም ሞት እንደዚሁም ሁሉ ኀጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ። ሕግ እስከ መጣ ድረስ ኀጢአት በዓለም ነበረና፥ ነገር ግን፥ ሕግ በሌለበት ጊዜ ኀጢአት አይቈጠርም። ነገር ግን፥ በአዳም መተላለፍ ምሳሌ ኀጢአትን ባልሠሩት ላይ እንኳ፥ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ አዳም ይመጣ ዘንድ ላለው ለርሱ አምሳሉ ነውና። ነገር ግን፥ ስጦታው እንደ በደሉ መጠን እንደዚያው አይደለም ባንድ ሰው በደል ብዙዎቹ ሞተዋልና፥

ነገር ግን፥ የእግዚአብሔር ጸጋና ባንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የሆነው ስጦታ ከዚያ ይልቅ ለብዙዎች በዛ። አንድ ሰውም ኀጢአትን በማድረጉ እንደሆነው መጠን እንደዚያው ስጦታው አይደለም ፍርድ ካንድ ሰው ለኵነኔ መጥቷልና፥ ስጦታው ግን በብዙ በደል ለማጽደቅ መጣ። በአንዱም በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሠ፥ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ። እንግዲህ ባንድ በደል ምክንያት ፍርድ ለኵነኔ ወደ ሰው ሁሉ እንደ መጣ፥ እንዲሁም ባንድ ጽድቅ ምክንያት ስጦታው ሕይወትን ለማጽደቅ ወደ ሰው ሁሉ መጣ። በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኀጢአተኞዎች እንደ ሆኑ፥ እንዲሁ ደግሞ በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ። እንዲሁ ደግሞ ጸጋ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተነሣ በጽድቅ ምክንያት ለዘለዓለም ሕይወት ይነግሥ ዘንድ፥ጸጋ ከመጠን ይልቅ በለጠ" እንዲል (ሮሜ ፭፣፲፪-፳፩)።

መርገም ቀረልን ማለት በአዳም ኃጢአት ምክንያት የመጣብን ፍዳ ቀረልን ማለት ነው። ይህ ከሆነ የምንጠመቀው ለምንድን ነው ከተባለ ልጅነትን ለማግኘት ነው። አሁን ያልተጠመቀ ሰው መርገምና ኃጢአት አለበት። መርገሙና ኃጢአቱ ግን ራሱ በነጻ ፈቃዱ የመረጠው ነው እንጂ ከአዳም የወረሰው አይደለም። አለመጠመቅ (ልጅነትን ማጣት ወይም አለማግኘት) ራሱ ኃጢአት ነውና። ስለዚህ ሰው ሲጠመቅ ከቁራኝነት ይላቀቃል፣ ከፍዳ ይነጻል የሚል ሐተታ ቢገኝ ራሱ በነጻ ፈቃዱ ካመጣው ፍዳና ቁራኝነት ይድናል ማለት ነው እንጂ ከአዳም ከወረሰው መርገም ይድናል ማለት አይደለም። ከአዳም የወረስነው መርገም በክርስቶስ ተሸሯልና። ሃይ. አበ. ፪፣፬ ሐተታ ላይ ወፅዐረ ዘሞት ፈትሐ የሚለውን ሊቃውንት ሲተረጉሙ "ጥንቱን ሰው ሲፀነስ በዘር በጽነት ምክንያት ነበር። ወይፈኑ አሐደ አሐደ እመላእክቲሁ እንዲል። ከሠራዊቱ አንድ አንዱን እየሰደደ በማኅፀን ያቆራኘው ነበር። ከተወለደም በኋላ ኃጢአት ሲያሠራው ጣዖት ሲያስመልከው ይኖር ነበር። ጌታ ግን መንገድ ለውጦበታል ሰውን በዘር በጽነት ምክንያት ይቆራኝ ነበር ጌታ ያለ ዘር ተፀንሶ ተወለደ። ኃጢአት ሲያሠራ ጣዖት ሲያስመልክ ይኖር ነበር በገዳም በሠለስቱ አርእስተ ኃጣውዕ ድል ነሥቶታል። ጌታ እንበለ ዘር እንደተወለደ እኛም በዕለተ ዓርብ ከኀጉ በፈሰሰው ጥሩ ውሃ ተጠምቀን ከሥላሴ እንወለዳለን። ከቁራኝነት እንላቀቃለን ከፍዳ እንድናለን ብለው ተርጉመውታል። ከዚህ ከፍዳ እንድናለን ማለቱ ባለመጠመቅ ከሚያጋጥመን ችግር ማለትም ልጅነትን ከማጣት፣ ገነትን ከማጣት እንድናለን ማለት ነው።

ክፍል ፮

ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ አብ ወልደ ማርያም ስለመሆኑ

በጊዜ ተዋሕዶ ሥጋ የቃልን ገንዘብ ሁሉ ገንዘቡ አድርጓል። አካላዊ ቃል ቅድመ ተዋሕዶ ወልደ አብ ብቻ ነበር። በጊዜ ተዋሕዶ ግን ወልደ አብ ወልደ ማርያምነትን ገንዘብ አደረገ። ስለዚህ ወልደ አብ ብቻ ሳይሆን ወልደ ማርያምም ነው። ወልድ ቅድመ ዓለም ከአብ ስለመወለዱ ነቢዩ ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ ገልጾታል። "ወለድኩከ እምከርሥ እምቅድመ ኮከበ ጽባሕ። ዓለም ሳይፈጠር አስቀድሞ ባሕርይ ዘእምባሕርይ አካል ዘእምአካል ወለድኩህ" እንዲል (መዝ. ፻፱፣፫ አንድምታ)። ባሕርይ ዘእምባሕርይ የሚለው ቃል ቃል እም ልብ ማለት መሆኑን መረዳት ይገባል። ባሕርይ የሦስቱ ኩነታት ተገናዝቦ ተብሎ የሚተረጎምበት ጊዜም አለ።

ባሕርይ አካል የሚገልጸው የአካል መሠረት ተብሎም ይተረጎማል። በዚህ ጊዜ የዚህ ባሕርይ ስሙ አይታወቅም። እንኳንስ የእግዚአብሔር የባሕርይ ስም የፍጡራን የባሕርይ ስምም እንደማይታወቅ ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በድርሳኑ አስተምሯል። "ኢታንክር ኦ ፍቁር በእንተ ዝንቱ ጎድግሰ ባሕርየ እግዚአብሔር ልዑል ለመልአክኒ ጥቀ ኢይትረከብ ስመ ባሕርይሁ። ወበእንተ ነፍስኒ ከማሁ ይመስለኒ። እስመ ብሂለ ነፍስ ኢይኤምር ኀበ ስመ ባሕርይሃ" እንዲል (ድርሳን ፪)። ቅድመ ዓለም ወልድ ከአብ የተወለደው ልደት ዘኢየኀልቅ ልደት ይባላል። ይኽውም ተመትሮ የሌለበት መሆኑን ለመግለጽ ነው። በእኛ ዘንድ እናት ልጅን ስትወልድ ልጅ ከእናት ማኅፀን ተለይቶ ይወጣል። በዚህ ጊዜ በህልውና መለየት (ተመትሮ) አለበት። ወልድ ከአብ ተወልደ ሲባል ግን ከህልውና ሳይለይ ስለሆነ ተመትሮ የለበትም። ዘኢየኀልቅ ልደት መባሉ አንደኛው ይህ ነው። ዘኢየኀልቅ ልደት መባሉ ሁለተኛው ሁልጊዜም ወልድ ወልድ ሲባል እንደሚኖር ለመግለጽ ነው።

ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ትንቢት "ወልድየ አንተ ወአነ ዮም ወለድኩከ" ብሏል (መዝ. ፪፣፯)። ይህ ለቅድመ ዓለሙ ልደት ይነገራል። ወልድየ አንተ ማለቱ የአብን ወላዲነት የወልድን ተወላዲነት ይገልጻል። ወአነ ዮም ወለድኩከ ማለቱም ይህንኑ የሚያጎላ አነጋገር ነው። በዚህ ጊዜ የዮም ትርጉም ከወትር ጋር ይገጥማል። እስመ ብሂለ ዮም ወትረ ብሂል እንዲል አፈወርቅ። ወትረ የሚለውም ኢየኀልቅ ልደቱ ካለው ምሥጢር ጋር ይገጥማል። ይህንን መተርጉማን "አሁን ሁለተኛ የሚወልደው ሆኖ አይደለም በምሳሌ ተናገረው እንጂ። ሰው ዘምቶ ያረጃል በልቶ ያፈጃል። ሕዝብን ሰብስቦ ልጁን አስጠርቶ ልጄ ዘምቶ ያረጀ በልቶ ያፈጀ ይሉሀል እኔ ነኝ። በርስቴ ውጣበት ውረድበት ብሎ ይሰጠዋል። እርሱም ወጣሁ ልጅ ነኝ ፈላሁ ጠጅ ነኝ ብሎ እግሩን ለጠጠር ደረቱን ለጦር ሰጥቶ ይዘምታል። በርስቱ ርስት በጉልቱ ጉልት ጨምሮበት ይመጣል። አባቱ በሰጠኸኝ ርስት ጉልት ጨምሬበት መጣሁ ይለዋል። እርሱም ቀድሞም ልጄ ዛሬም ልጄ ይልቅስ የዛሬው ይበልጥ ይለዋል። በዚህ አምሳል ወልድም ነፍሳትን በገነት አድርጎ ባረገ ጊዜ አብ ልጄ ነህ አለው" ብለው ገልጸውታል።

በሌላ አገላለጽ ወልድየ አንተ የሚለው ወልድ ቅድመ ዓለም ከአብ መወለዱን፣ ወአነ ዮም ወለድኩከ ማለቱ ሥጋ በቃል ርስት መወለዱን (ልጅነትን ገንዘብ ማድረጉን) ይገልጻል። ይህንንም ዮሐንስ አፈወርቅ በድርሳኑ ገልጾታል። "ወካዕበ ይቤ አነ እከውኖ አባሁ ወውእቱ ይከውነኒ ወልድየ። ዝኒ ከማሁ ዓዲ በእንተ ትስብእቱ። ወብሂሎቱሰ ወልድየ አንተ ወአነ ዮም ወለድኩከ ዝኒ በእንተ ልደቱ እምቅድመ ዓለም እምኔሁ። ወብሂሎቱሰ ዮም ወለድኩከ ዝኒ ካዕበ በእንተ ትስብእቱ። እስመ ፈጣሪ ሎቱ ስብሐት ሀሎ እምቅድመ ዮም ወጊዜ። አላ ዘንተ ይቤ በእንተ ሥጋዊ ወልዱ" እንዲል (ድርሳን ፪፣ በተጨማሪ ዕብ.፩፣፭ ትርጓሜን ይመልከቱ)። ወአነ ዮም ወለድኩከ ለሥጋ ሲነገር በቃል ርስት መሆኑን ልብ ማድረግ ይገባል። ንስጥሮስ ወልደ አብን ማርያም አልወለደቸውም። ወልደ ማርያምን አብ አልወለደውም ብሎ የምንታዌ ትምህርትን አስተምሯል። ለእርሱ ትምህርት ምላሽ የሰጡት ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ "ድንግልኒ ወለደት ዘኢዘአሃ መለኮተ በዘዘአሃ ሥጋ ምስለ ዘዘአሃ ሥጋዊ። አብኒ ወለደ ዘኢዘአሁ ሥጋ በዘዘአሃ ሥጋዊ ምስለ ዘዘአሁ ኃይል ዘህሉና አምላክ" ብሏል። ትርጉሙም ድንግል ለእርሷ በተገባ ሥጋ የእርሷ በሆነ ሥጋ የእርሷ ያልሆነውን መለኮት

ወለደችው። አብም የባሕርይው ያልሆነውን ሥጋ የእርሱ በሆነ መለኮት ወለደው ማለት ነው። መምህረ ዓለም ቅዱስ ቄርሎስ እንደተናገረው በጊዜ ተዋሕዶ የሥጋ ገንዘብ ለቃል የቃል ገንዘብ ለሥጋ ሆኗል። ቅድመ ዓለም የቃል ገንዘብ የሆነው ወልደ አብነት ለሥጋም ገንዘቡ ሆኗል። ስለዚህም ወልደ አብ ተብሎ ይጠራል። ድንግል ማርያም ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ስለወለደችውም ወልደ ማርያም ይባላል። ወልደ አብም ወልደ ማርያምም የሚባለው ያው አንዱ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ልብ ማድረግ ይገባል።

ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን